መልእክት አሥራ-አንድ

## በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ጌታን የመፍራት

## ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ምሳ. 1፡1፣ 7፤ 2፡4-5፤ 3፡5-10፤ 8፡13፤ 9፡10፤ 10፡27፤ 14፡2፣ 26-27፤ 15፡16፣ 33፤ 16፡6፤ 19፡23

I. **ለሰው ተገቢ የሆነ የስብዕና ሕይወትን ለመኖር የመጀመሪያው መርህ ጌታን መፍራቱ፣ ጌታን ማክበሩ ነው። ጌታን መፍራት ማለት እርሱን ላለማሳዘን፣ መገኘቱን ላለማጣት እና በሚቀጥለው ዘመን እርሱን እንደ ሽልማታችን አለመቀበልን መፍራት ነው፤ በዚህ ዘመን የጌታን ፈገግታ በሚቀጥለው ዘመን ደግሞ ሽልማቱን እንዳናጣ መፍራት አለብን—ምሳ. 1፡1፣7፤ ኤፌ. 4፡30፤ 2 ቆሮ. 5፡9-10፡-**

ሀ. ጌታን መፍራት ማለት በሁሉ ነገር እርሱን ማሰብ እና ለእርሱ ትኩረት መስጠት፣ እርሱ የፈጠረን ድንቁ አምላክ መሆኑን በፍፁም አለመርሳት (ኢሳ. 43፡7) ማለት ነው፤ እግዚአብሔርን መፍራት ክፉ ነገሮችን ከማድረግ ያስቆመናል፤ በሌሎች መከራዎች እንድንነካ እና ምህረት እና ርኅራኄ እንድናሳያቸው ያደርገናል።

ለ. ጌታን መፍራት ከኃጢአቶች መሸሽ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም እኔነትን መቃወም ነው፤ጌታን መፍራት ኃጢአት ሠራን ወይም ዓለማዊ ሆንን ብሎ መፍራት ብቻ ሳይሆን የምናደርገው ነገር ከጌታ ሳይሆን ከራሳችን የመነጨ ነው ብሎ መፍራት ነው—ማቴ. 16፡24፤ 2 ቆሮ. 4፡5።

ሐ. እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው፣ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው፤ እውቀት፣ ጥበብ እና ማስተዋል ከእግዚአብሔር ይመጣሉ። እርሱን ከፈራነው እና ካከበርነው እነዚህ ነገሮች ሃብቶቻችን ይሆናሉ—ምሳ. 1፡1፣ 7፤ 2፡4-5፤ 3፡5-10፤ 8፡13፤ 9፡10፤ 10፡27፤ 14፡2፣ 26-27፤ 15፡16፣ 33፤ 16፡6፤ 19፡23።

II. **ኢሳይያስ የያህዌ መንፈስ—የጥበብ መንፈስ፣ የማስተዋል መንፈስ፣ የምክር መንፈስ፣ የኃይል መንፈስ፣ የእውቀት መንፈስ፣ ያህዌን የመፍራት መንፈስ—በክርስቶስ ላይ እንደሚያርፍ ትንቢት ተናገረ—ኢሳ. 11፡1-2፡-**

ሀ. መንፈስ ሁልጊዜ ከጌታ ጋር ነበረ፣ ከእርሱም ጋር አንድ ነበረ፤ በመንፈስ ተመላለሰ እንዲሁም በመንፈስ ውስጥ፣ ከመንፈስ ጋር፣ በመንፈስ እና በመንፈስ በኩል የሆነ ሕይወትን ኖረ፤ ኢሳይያስ 11፡2 በጌታ የስብዕና ሕይወት መንፈስ ከላይ ከተጠቀሱት ሰናይ ባህርያት ሁሉ ጋር ተገልጧል—ሉቃ. 4፡1፣ 14፤ 10፡21፤ ዮሐ. 1፡32፤ ማቴ. 12፡28።

ለ. በስብዕና ኑሮው፣ ኢየሱስ አክባሪና ተገዢ በሆነ ጌታን የመፍራት መንፈስ የተሞላ ነበረ፤ በተጨማሪም ጌታን በመፍራት ደስ ይሰኝ ነበረ፤ አሁን በትንሣኤው እርሱ ያህዌን እንደመፍራት መንፈስ፣ በቃላት መግለጥ የማይቻለውን የኢየሱስን የስብዕና ኑሮ እና አገልግሎት የሚያካትት፣ ሁሉን-ያካተተ፣ በተትረፈረፈ መንገድ አቅርቦት የሚሰጥ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው—ኢሳ. 11፡2-3፣ ፊልጵ. 1፡19፡-

1. የኢየሱስን ያህል እግዚአብሔርን የፈራ ማንም ሰው የለም፤ የእግዚአብሔርን የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በማከናወኑ፣ ጌታ ኢየሱስ ምንም ነገር ከራሱ እንዳላደረገ (ዮሐ. 5፡19)፣ የራሱ ሥራ እንደሌለው (4፡34፤ 17፡4)፣ የራሱን ቃል እንዳልተናገረ (14፡10፣ 24)፣ ሁሉንም ነገር ያደረገው በራሱ ፈቃድ እንዳልሆነ (5፡30) እና የራሱን ክብር እንዳልፈለገ (7፡18) ነግሮናል።
2. ኢየሱስ ሁሉን ነገር በእግዚአብሔር ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና ለእግዚአብሔር ያደረገ ኑሮን ኖረ፤ እግዚአብሔር በኑሮው ውስጥ ነበረ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ነበረ፤ ይህ በኢየሱስ ያለው እውነታ ነው (ኤፌ. 4፡20-21)፤ ጌታን እንደ እውነታ መንፈስ የእርሱን ለአብ የመገዛት ሕይወት እና የእርሱን የመታዘዝ ሕይወት ወደ መለማመድ እውነታ እንዲመራን መጠየቅ አለብን(ዮሐ. 16፡13፤ ፊልጵ. 2፡5-11)።
3. ዕለት በዕለት ሙሉበሙሉ እና ፍጹም በሆነ መንገድ ለአብ መከፈትና የጌታ ኢየሱስን የስብዕና ኑሮና አገልግሎት ባካተተው ጌታን የመፍራት መንፈስን በሆነውን ከሞት በተነሣው ክርስቶስ ሁሉን-እንዳካተተው መንፈስ እንዲሞላን መጠየቅ አለብን—ሉቃ. 11፡5-13።

III. **እግዚአብሔርን መፍራት በእርሱ መታመን ነው—ምሳ. 3፡5-8፣ 26፤ 16፡1፣ 9፣ 20፣ 33፤ 19፡21፣ 30፡5-6፡-**

ሀ. ምሳሌ 3፡5-8 በሙሉ ልባችን በጌታ እንድንታመን እና በራሳችን ማስተዋል እንዳንደገፍ ያዝዘናል፤ በመንገዳችን ሁሉ ለእርሱ እውቅና መስጠት አለብን፣ እርሱም መንገዳችን ያቀናልናል፤ በራሳችን አስተያየት ጠቢብ መሆን የለብንም፤ ጌታን መፍራትና ከክፉ መራቅ አለብን፤ ይህ ለሥጋችን ፈውስ ለአጥንታችንም ጠገን ይሆንልናል።

ለ. "በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው። በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ፣ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፣ በድርቅ ዓመትም እንደማይሠጋ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል።"—ኤር. 17፡7-8፡-

1. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት፣ በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ ዛፍ ነው፣ ይህም ውኃ እግዚአብሔርን እንደ ሕያው ውኃዎች ምንጭ ያመለክታል—2፡13።
2. ዛፍ የሚያድገው በወንዝ አጠገብ የውኃውን ብልጥግናዎች ሁሉ በመውሰድ ነው፤ ይህ በእደላው የሚከናወነው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ስዕል ነው፤ መለኮታዊውን እደላ ለመቀበል፣ እኛ እንደ ዛፎቹ እግዚአብሔርን እንደ ውኃው መምጠጥ አለብን—ተዛ. 1 ቆሮ. 3፡6።
3. እንደ ዛፎች ወደ ሆንነው ወደ እኛ ውስጥ የታደለው አቅርቦት የሚሰጠው እግዚአብሔር ብልጥግናዎች በእግዚአብሔር መለኮትነት ያቀናብረናል፣ ወደ እግዚአብሔር ልክም እንድናድግ ያደርገናል (ቆላ. 2፡19)፤ በዚህ መንገድ እኛ እና እግዚአብሔር አንድ አይነት ንጥረ-ነገር፣ ይዘት፣ ቅንብር እና መገለጥ ኖሮን አንድ እንሆናለን (ራእ. 4፡3፤ 21፡11)።

ሐ. ቃልን የሚያዳምጥ መልካም ነገርን ያገኛል፤ በእግዚአብሔር የታመነ ምስጉን ነው (ምሳ. 16፡20)። እግዚአብሔር መታመናችን ይሆናልና፣ እግሮቻችንንም እንዳይጠመዱ ይጠብቀናል (3፡26)።

መ. እግዚአብሔርን የሚወዱ ወደ እግዚአብሔር ቃል በመምጣት እግዚአብሔርን መፍራትን ይማራሉ (2፡3-5፤ ዮሐ. 5፡39-40)፤ እግዚአብሔርን እንደ መፍራታችን ማረጋገጫ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንድንጣበቅ እና የእግዚአብሔርን ቃል እንድንታዘዝ ታዝዘናል (ዘዳ. 6፡2)።

## IV. ጌታን መፍራት ማለት እርሱን እናከብረዋለን ማለትም ጭምር ነው፡-

ሀ. ምሳሌ 3፡9-10 ጌታን ከሃብታችን፣ ከፍሬአችን ሁሉ በኵራት ማክብር እንዳለብን ይነግረናል፤ ያኔ ጐተራችን በእህል ይሞላል፣ መጥመቂያችን በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።

ለ. ለወደፊታችን ሃብትን ለማከማቸት ብለን ተጨማሪ ገንዘብን የምንሠራ ሰዎች መሆን የለብንም፤ ከምንሠራው ቢያንስ አንድ አሥረኛው፣ በኩራቱ ለእግዚአብሔር መሰጠት አለበት፤ እግዚአብሔር የሰጠንን ነገሮች በመስጠት ሁልጊዜ ለጋሶች መሆን አለብን፤ ይህ እግዚአብሔርን ያከብረዋል—ሚል. 3፡7-12፤ 2 ቆሮ. 9፡6-8።

ሐ. ስሙን እንፈራ ዘንድ ልባችንን ነጠላ እንዲያደርግልን ጌታን መጠየቅ አለብን፤ "እግዚአብሔር ሆይ መንገድህን አስተምረኝ፤ በእውነትህም እሄዳለሁ፤ ስምህን እፈራ ዘንድ ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ።"—መዝ. 86፡11 (አ.መ.ት)።

መ. "በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን ማንጻት አለብን።" እግዚአብሔርን መፍራት እዚህ ጋር የእግዚአብሔር ያልሆኑ ነገሮችን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ነገሮችን ለመንካት አለመድፈር ነው—2 ቆሮ. 7፡1፤ 6፡17።

ሠ. በክርስቶስ ፍርሃት ውስጥ መሆን ማለት ራስ የሆነውን እርሱን ላለማሳዘን መፍራት ነው፤ ይህ አንዳችን ለሌላችን መገዛትን ያካትታል፤ ጌታን በፍርሃት ማገልገል አለብን፤ ያኔ በጌታ ደስ ለመሰኘትና ጌታን ለመደሰት ጌታን እንወደዋለን—ኤፌ. 5፡18-21፤ ምሳ. 2፡11-12፤ ዕብ. 12፡28።

ረ. በክርስቶስ የሆንን አማኞች በሙሉ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ስለምንቀርብ፣ እኛ ሁላችን ተገቢ የሆነ የጌታ ፍርሃት ሊኖረን ያስፈልጋል፤ በዚያን ጊዜ ስለ ዘላለማዊ ድነት ሳይሆን ስለ መግቦተ ዘመናዊ ሽልማታቸው ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ አማኞች ላይ ይፈርዳል—2 ቆሮ. 5፡10፤ 1 ቆሮ. 4፡4-5፤ 3፡13-15፤ ሮሜ. 14፡10።

ሰ. እግዚአብሔርን መፍራት እድሜን ማርዘሚያ መንገድ ነው (ምሳ. 10፡27)፤ እግዚአብሔር የሚፈሩትን ሰዎች ይወዳቸዋል፣ ይጠብቃቸዋል፣ ይባርካቸዋል፣ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል (መዝ. 103፡11፣ 13፣ 17፤ 85፡9፤ 60፡4፤ ምሳ. 14፡26-27፤ መዝ. 115፡12-13፤ 34፡9፤ 111፡5)።

ረ. ኖህ (ዕብ. 11፡7)፣ አብርሃም (ዘፍ. 22፡12)፣ ዮሴፍ (42፡18)፣ ዳዊት (መዝ. 2፡11-12፤ 5፡7)፣ ነህምያ (ነህ. 1፡11፤ 5፡9፣ 15) እና የቀደሙችው ቤተ ክርስቲያን (ሐዋ. 9፡31) እግዚአብሔርን የመፍራት ምሳሌዎች ናቸው።

## V. ቅዱስ የሆነ የጌታ ፍርሃት፣ ለኢኮኖሚው መከናወን እግዚአብሔርን ወደ እኛ ውስጥ ለማደል እንደ የሕይወት ምንጭ (ምሳ. 14፡27) እና እንደ የሕይወት ዛፍ (11፡30) የደስታ ምንጭ ነው (መዝ. 2፡11)፡-

ሀ. እግዚአብሔርን መፍራት ሰው ከሞት ወጥመድ ይድን ዘንድ የሕይወት ምንጭ ነው፣ ጌታን መፍራት፣ በጌታ መታመን፣ በጌታ ስም ውስጥ መሸሸግ በሕይወት ጎዳናዎች መጓዝ ነው (ምሳ. 2፡19፤ 5፡6፤ 10፡17፤ 14፡27፤ 19፡23፤ መዝ. 16፡11)፤ የሕይወት ጎዳናዎች የሕይወት ዛፍ ጎዳናዎች ናቸው፣ የዚህም ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር ነው (ምሳ. 3፡13፣ 18፤ 11፡30፤ 13፡12፤ 15፡4)።

ለ. እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት ይመራል፤ ወደ ሕይወት የሚመራው የተገደበው መንገድ (የብዙዎች ሳይሆን የጥቂቶች መንገድ) ነው፤ የሕይወት ጎዳናዎች በእግዚአብሔር ውስጥ እንድንኖር በዚህም ሕይወትን እንድንነካና እንድናገኝ ነው፤ እነዚህ ጎዳናዎች ወደ እርሱ ውስጥ እንድንገባ እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያስቀመጣቸው መንገዶች ናቸው—19፡23፣ ማቴ. 7፡13-14፤ ምሳ. 84፡5።

ሐ. የሞት መንገዶች የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ መንገዶች ናቸው፣ ምንጫቸውም ሰይጣን ነው፣ የሚገለጠውም በእኔነታችን ነው፤ በእኔነት ውስጥ መኖር የእግዚአብሔር መገኘት የሌለው መሆን፣ በጨለማ መንገዶች መመላለስ እና ሕይወት አልባ መሆን ማለት ነው—ምሳ. 2፡13፤ 3፡5-7፤ 14፡12፤ 16፡25፤ ኤፌ. 5፡2፣ 8-9።

**VI. ለእኛና ከእኛም በኋላ ለልጆቻችን መልካም እንዲሆንልን ለዘላለም እንፈራው ዘንድ አንድ ልብና አንድ መንገድ እንደሚሰጠን እና ከእርሱ ፈቀቅ እንዳንል መፈራቱን በልባችን ውስጥ እንደሚያኖር ቃል ገብቶልናል—ኤር. 32፡39-40፦**

ሀ. እኛ፣ በእግዚአብሔር የተመረጥን ሕዝብ፣ አንድ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል—ይህም እግዚአብሔርን ለመውደድ፣ እግዚአብሔርን ለመፈለግ፣ እግዚአብሔርን ለመኖር እና የእርሱ መገለጥ እንሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ለመቀናበር ነው—እንዲሁም አንድ መንገድ—ሦስትንዱ አምላክ ከመለኮታዊው አቅም ጋር እንደ ውስጣዊ የሕይወት ሕግ ሊኖረን ያስፈልጋል—ቁ. 39፤ 31፡33-34፤ ዮሐ. 14፡6፤ ሮሜ. 8፡2።

ለ. ይህ አንድ ልብ እና አንድ መንገድ በአንድ ልብ መሆን ናቸው (ሐዋ. 1፡14፤ 2፡46፤ 4፡24፤ ሮሜ. 15፡6)፤ ክፍፍሎች የሚመጡት ከክርስቶስ ውጭ ለሆነ ነገር ልብ ሲኖረን እና ከክርስቶስ ውጭ ሌላ መንገድ ስንወስድ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ዘላለማዊ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳንን አድርጓል፤ እግዚአብሔር ከእኛ ዘወር የማይለው በዚህ ኪዳን ምክንያት ነው፣ እኛም ከእርሱ ዘወር እንዳንል መፈራቱን በልባችን ያኖራል—ኤር. 32፡40።

መ. እግዚአብሔርን ስንፈራ፣ መምረጥ ስላለብን መንገድ እግዚአብሔር ያስተምረናል፣ የእግዚአብሔርን የቅርብ የሆነ ምክርና ኪዳኑን ማወቅ እንችላለን፤ የኪዳኑ መገለጥ ሊኖራቸው የሚችለው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ብቻ ናቸው፣ ለሚፈሩትም የቅርብ የሆነ ምክሩን ይሰጣቸዋል—መዝ. 25፡12፣ 14።

**VII. ጌታን መፍራት እና ጌታን መውደድ የኃጢአቶቻችን ይቅርታ ሁለት ድንቅ ውጤቶች ናቸው፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ይቅርታ ሰውን ደፋር እና ግድ-የለሽ እንዲሆን አያደርገውም፤ የእግዚአብሔር ይቅርታ ጸጋ ሰውን ጌታን ወደ መፍራት ያመጣዋል፤ "[ትፈራ ዘንድ] ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና"—130፡4።

ለ. የእግዚአብሔር ይቅርታ ጸጋ እግዚአብሔርን እንድንወደው ያደርገናል፤ በሉቃስ ላይ ያለችው ኃጢአተኛ ሴት ጌታን አብዝታ የወደደችው ከጌታ በብዙ ይቅርታን ስላገኘች ነበረ—7፡39-50።

ሐ. ጌታ አብዝቶ ይቅር ሲለን፣ አብዝተን እርሱን እንፈራዋለን፤ አብዝተን ስንፈራው፣ አብዝተን እንወደዋለን፤ በአሉታዊ ጎኑ፣ ስለምንወደው እርሱን የማያስደስቱትን ነገሮች ከማድረግ እንቆጠባለን፤ በአዎንታዊ ጎኑ፣ ስለምንወደው እርሱን የሚያስደስተውን ነገሮች እናደርጋለን።

**VIII. ምሳሌ 31 ሁለት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ምሳሌዎችን ያቀርብልናል፤ በአንድ መልኩ ልክ እንደ ጌታ፣ ለመግዛት ስልጣን ያለን ሆነን እንደ ንጉሥ፣ ንጉሣዊ ሰው መሆን አለብን፤ በሌላ መልኩ በእግዚአብሔር ቤት የቅዱሳንን ፍላጎት እንዴት ማዘጋጀት፣ ማስተዳደር፣ መንከባከብ እና አቅርቦት መስጠት እንዳለብን በማወቅ ዋጋዋ የከበረ ሴት መሆን አለብን፦**

ሀ. ምሳሌ 31፡3 እስከ 9 ስለሚገዛ ንጉሥ—ወይን ስለማይጠጣ ነገር ግን ስለሌሎች መብት የሚናገርና ፍትህን ስለሚያገለግል (ክርስቶስን እና ድል-ለሺዎቹን በምሳሌ በማሳየት)—ይናገራል፤ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ብቻ መግዛት ይችላል፦

1. ጌታችን ሙሉበሙሉ በእግዚአብሔር መገደብ ሥር ነበረ፤ ስለዚህም ለእግዚአብሔር መግዛት ችሎ ነበረ፤ በእግዚአብሔር መገደብ ከቻልን እና ራሳችን ካስወገድን፣ ለእግዚአብሔር መግዛት እንችላለን።
2. በሰዎች ላይ በመግዛቱ፣ ንጉሡ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃል መማር፣ መመራት፣ መገዛት፣ እና ቁጥጥር ሥር መሆን አለበት፤ በአብያተ-ክርስቲያናት ባሉ ሽማግሌዎችም መርሁ ያው መሆን አለበት—ዘዳ. 17፡14-20፦
   ሀ. ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደር ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ዳግም መቀናበር አለባቸው፤ ከዚህም የተነሣ፣ በእግዚአብሔር አገዛዝ፣ በእግዚአብሔር መግዛት እና ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ።
   ለ. ያኔ ቅፅበታዊ በሆነ መንገድ፣ እግዚአብሔር በውሳኔዎቻቸው ውስጥ ይሆናል፣ ሽማግሌዎችም የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች ለማስተዳደር እግዚአብሔርን ይወክላሉ፤ እንዲህ ዓይነቱ አስተዳደር የእግዚአብሔር አስተዳደር (ቲኦክራሲ) ነው።

ለ. ምሳሌ 31፡10 እስከ 31 ዋጋዋ የከበረውን (12፡4፤ 19፡14፤ ሩት 3፡11)—ጠቢብ፣ ቸር፣ ትጉህ እና ችሎታ ያላት እንዲሁም ቤተሰቦቿን ማስተዳደር እና ለቤተሰቦቿ አቅርቦትን መስጠት የምትችል—ሴትን ይገልፃል። "ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል"(ምሳ. 31፡10)፤ ክብሯ ከአቻዎቿ ሁሉ ይበልጣል (ቁ. 29)፤ ይህች ልባም ሴት ቤተ ክርስቲያን እና ጌታን የሚወዱ ቅዱሳንን ትወክላለች፡-

1. ዋጋዋ የከበረ ሴት ዋና መለያ ባህሪ ጌታን መፍራቷ ነው (በፍርሃት-በተሞላ አክብሮት ጌታን በማክበር ማምለክ፣ መታዘዝ፣ ማገልገል እና መታመን)፤ "ውበት ሐሰት ነው፣ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች"—ቁ. 30።
2. ዋጋዋ የከበረች ሴት ባል ልብ በእርስዋ ይታመናል፤ "ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም" (ቁ. 12)፤ "ባልዋ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ በበር የታወቀ ይሆናል" (ቁ. 23)።
3. እንዲህ ያለችው ዋጋዋ የከበረና ልባም ሴት ከጌታ ዘንድ ለባሏ እንደ ዘወድ ናት (12፡4)፤ ልጆቿና ባሏ ተነሥተው የተባረከች ብለው ይጠሯታል (31፡28)፤ ባሏም ከሁሉ ትበልጫለሽ ብሎ ያመሰግናታል (ቁ. 29)።
4. ባል በራሱ ዓይን የሚስቱን "በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮ" ማየት መቻል አለበት፤ መዋቢ ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት ሳይሆን "ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው" መሆን አለበት—1 ጴጥ. 3፡1-4።
5. ተገቢ በሆነው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እኅቶች "በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፣ መልካም በማድረግ እንጂ በሽሩባና በወርቅ ወይም በዕንቍ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ"፤ እግዚአብሔርን መፍራት እግዚአብሔርን ለሚያመልክ ሰው እንደሚገባ ወደ እግዚአብሔር ያለ ፍርሃት፣ እግዚአብሔርን ማክበር ነው—1 ጢሞ. 2፡9-10።
6. "ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፣ ባሎቻቸውን የሚወዱ፣ ልጆቻቸውን የሚወዱ፣ ራሳቸውን የሚገዙ፣ ንጹሖች፣ በቤት የሚሠሩ፣ በጎዎች፣ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ [ይመክሯቸው]" ዘንድ በእድሜ ከፍ ያሉ ሴቶች በባሕሪያቸው፣ በአካሄዳቸው የተከበሩ መሆን አለባቸው—ቲቶ 2፡3-5።

ሐ. ድል ከመንሣት አኳያ እንደ ንጉሥ መሆን አለብን፤ ጌታን ከመውደድ አኳያ ዋጋዋ እጅግ የከበረ ሴት መሆን አለብን፤ እንዲህ መሆናችን በጌታ ፊት ዋጋ እና ክብር እንዲኖረን ያደርገናል።

*© 2020 Living Stream Ministry*